# በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

## የDPS የ SchoolChoice ምዝገባ አሰራር የሚሰራው እንዴት ነው?

የ SchoolChoice የተዘጋጀው ለቀጣዩ ዓመት ወደ አዲስ ትምህርት ቤት መግባት ለሚፈልጉ ወይም ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች በተለይም "ለሚሸጋገሩ" ተማሪዎች ነው። ሁሉም አዲስ ገቢ የECE ተማሪዎች ማመልከቻ መሙላት አለባቸው። ልጅዎ በአሁኑ ወቅት የክፍል ደረጃው ከአፀደ ህጻናት እስከ 11ኛ ክፍል ከሆነ እና ለ2023-24 የትምህርት አመት በአሁኑ ትምህርት ቤቱ የሚቀጥል ከሆነ የ SchoolChoice ማመልከቻ መሙላት አይጠበቅብዎትም።* የ SchoolChoice የሚሰራው በሚከተለው መልኩ ነው፥

1. በመጀመሪያ የተመራጭ ትምህርት ቤቶች የምዝገባ መመሪያ በመመርመር፣ ትምህርት ቤት ፈላጊ በመጠቀም እና የሚፈልጓቸውን ትምህርት ቤቶች በማነጋገር የDPS ትምህርት ቤቶችን ያጥኑ።
2. ለልጅዎ የመጀመሪያ ደረጃ ምርጫዎች ቅደም ተከተል በመስጠት በ SchoolChoice ማመልከቻ ላይ በደረጃ ያስቀምጧቸው። እስከ 12 ትምህርት ቤቶች ድረስ የተለያዩ ምርጫዎችን እንዲዘረዝሩ እንመክርዎታለን።
3. በዙር 1 ሂደት ወቅት የ SchoolChoice ማመልከቻዎን በኦንላይን ያስገቡ። የ2023-24 የትምህር ዓመት የ SchoolChoice ሂደት ከጃኑዋሪ 13, 2023 በ 10 a.m. ሰዓት ጀምሮ ፌብሩዋሪ 14, 2023 በ 4 p.m. ሰዓት ያበቃል።
4. የ SchoolChoice የልጅዎን የመጀመሪያ ደረጃ ምርጫዎች ከእያንዳንዱ ትምህርት ቤት የምዝገባ ቅደም ተከተሎችና ያለው ቦታ ጋር ያጣምራል። ለሁሉም ተማሪዎች በጥቅሉ የየትኛውን ትምህርት ቤት ወንበር እንደሚያገኙ የሚወስንላቸው የሎተሪ ቁጥር ይሰጣቸዋል።

ለተማሪዎች ባለው ወንበር ላይ ተመስርቶ በከፍተኛ ደረጃ የሚመርጡት ትምህርት ቤት ወንበር ይሰጣቸዋል። ይህ በማርች መጨረሻ ይገለጽልዎታል። ለትምህርት ቤቶች በምርጫዎ ቅደም ተከተል መሰረት ደረጃ ይስጧቸው።

*ማስታወሻ፥ በአንዳንድ ሁኔታዎች በአሁኑ ትምህርት ቤታቸው መቆየት የሚፈልጉ ተማሪዎች የ SchoolChoice ማመልከቻቸውን እንዲያስገቡ ይጠየቃሉ። ይህ ከECE-8ኛ ወይም ከ6-12ኛ ክፍል ተማሪዎችን ሊያጠቃልል ይችላል። ጉዳዩ ይህ ከሆነ ለቤተሰቦች ከዙር 1 በፊት በDPS ይገለጽላቸዋል።*

## በሰጠሁት ደረጃ ቅደም ተከተል ላይ ተመስርቶ ወደመረጥኩት ትምህርት ቤት የምገባበት የተሻለ እድል አለኝ?

ምንም የሚስጥር ቀመር የለም! የተለያዩ ትምህርት ቤቶችን በዝርዝር እንዲያስቀምጡ እንመክራለን፣ ሆኖም እጅግ አስፈላጊው ነገር ለትምህርት ቤቶቹ እንደየ ምርጫዎ ቅደም ተከተል በደረጃ ማስቀመጥ ነው። የመጀመሪያ ደረጃ ምርጫዎን የማያገኙ ከሆነ የምርጫ ሲስተሙ ወደ ቀጣዩ ደረጃ ምርጫዎ ያልፋል። አንድ ትምህርት ቤት በማመልከቻዎ ላይ በሰጡት ደረጃ ላይ ትኩረት ያደርጋል የሚለው የተሳሳተ ግንዛቤ ነው። ትምህርት ቤቶች እርስዎ የሰጧቸውን ደረጃዎች የማይመለከቱ ከመሆኑም በተጨማሪ ቁጥር 1 ደረጃ የሰጧቸውን ተማሪዎች ብቻ መርጠው የሚወስዱበት አማራጭ የላቸውም።
ምደባዎች የሚካሄዱት ተማሪው ለትምህርት ቤቱ በሰጠው ቅድሚያ ምድብ እና በተማሪው የሎተሪ ቁጥር ላይ ተመስርተው ነው። ለምሳሌ፣ ለአንድ ትምህርት ቤት በዝርዝሩ ላይ 3ኛ ደረጃ የሰጠ ተማሪ ለዚህ ትምህርት ቤት ተማሪው በመጀመሪያ ቅድሚያ ምድብ ስር የሚመደብ ከሆነ እና/ወይም ከፍተኛው የሎተሪ ቁጥር ከደረሰው ለዚሁ ትምህርት ቤት 1ኛ ደረጃ ከሰጠ ተማሪ ቀድሞ ትምህርት ቤቱ ሊቀበለው ይችላል።

## ማመልከቻዬን ከ SchoolChoice የመጨረሻው ቀን ይልቅ በመጀመሪያው ቀን ባስገባ ትምህርት ቤት የማግኘት የተሻለ እድል አለኝ?

አይደለም፣ በዙር 1 የ SchoolChoice ሂደት ወቅት ውስጥ የሚገቡ ማመልከቻዎች በእኩል ደረጃ ይስተናገዳሉ። ቀደም ብለው ለሚገቡ ማመልከቻዎች ቅድሚያ አይሰጥም።

## የምርጫ ሂደቱ ተማሪዎችን ከትምህርት ቤቶች ጋር የሚያዛምደው እንዴት ነው?

የዙር 1 ማብቃትን ተከትሎ ሁሉም ማመልከቻዎች ከገቡ በኋላ የምርጫ አልጎሪዝሙ ለሁሉም ተሳታፊ ተማሪዎች በጥቅሉ ከ1 እስከ 1 ሚሊዮን መካከል ካሉት ቁጥሮች ውስጥ የሎተሪ ቁጥር ይመድብላቸዋል። ለተማሪዎች በተጨማሪም በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት በተገለጹ በቅድሚያ የተወሰኑ የቅድሚያ ምድቦች ላይ ተመስርቶ ለእያንዳንዱ ትምህርት ቤት የቅድሚያ ደረጃ ይመደብላቸዋል።

ከዚያም አልጎሪዝሙ ለተማሪዎች በተመደበላቸው የሎተሪ ቁጥር ላይ ተመስርቶ ለተማሪዎች ደረጃ ይሰጥና በእያንዳንዱ የቅድሚያ ምድብ ስር ይመድባቸዋል። ይህ ለእያንዳንዱ ትምህርት ቤት እያንዳንዱ የክፍል ደረጃ የተማሪዎች የቅደም ተከተል (ደረጃና ምደባ) ዝርዝር ያዘጋጃል። ከዚያም ሲስተሙ ለተማሪዎች በዝርዝሩ ስር በተቀመጡበት ቅደም ተከተል ላይ ተመስርቶ ወንበር ይመድብላቸዋል፤ ከዚያም ሲስተሙ ለሁሉም ወንበር ላልተመደበላቸው ተማሪዎች በተሰጣቸው ደረጃና ምደባ ቅደም ተከተል ላይ ተመስርቶ የተጠባባቂ ዝርዝር ያዘጋጃል። ሲስተሙ የተዘጋጀው የመጀመሪያ ደረጃ ምርጫቸው የሆነ ትምህርት ቤትን የሚያገኙ ተማሪዎችን ብዛት ለማሳደግ ታስቦ ነው።

## ትምህርት ቤት ፈላጊ (School Finder) ምንድን ነው?

እዚህ ላይ ላይ የሚገኘው የትምህርት ቤት ፈላጊ ለDPS ቤተሰቦች የኦንላይን፣ ለሞባይል ተስማሚ የትምህርት ቤት መፈለጊያ መሳሪያ ነው። እዚህ ላይ ለእርስዎ አስፈላጊ የሆኑ የትምህርት ቤት ባህሪያትን ያስገቡ እና ምን ያክል ለእርስዎ ተፈላጊ መስፈርት ይቀርባሉ በሚለው ላይ ተመስርቶ ደረጃ የተሰጣቸው የሚዛመዷቸው ትምህርት ቤቶች ዝርዝር ይመጣልዎታል። በተጨማሪ በአድራሻ ወይም በቀላሉ የፊደል ቅደም ተከተል ዝርዝርን በመጠቀም መፈለግ ይችላሉ። ለልጅዎ ፍላጎቶች በጥሩ ሁኔታ የሚጣጣሙ ትምህርት ቤቶችን መወሰን በ SchoolChoice ማመልከቻዎ ለሚመርጧቸው ትምህርት ቤቶች ደረጃ በሚሰጡበት ወቅት ይረዳዎታል።

## የ"ሚሸጋገር" ተማሪ ማለት ምንድን ነው?

በአብዛኞቹ ሁኔታዎች የሚሸጋገር ተማሪ ማለት በአሁኑ ትምህርት ቤቱ ወይም ፕሮግራሙ ውስጥ የሚገኘውን ከፍተኛውን የክፍል ደረጃ ያጠናቀቀ ተማሪ ማለት ነው። ለምሳሌ፣ አሁን ትምህርቱን በECE-5 እየተከታተለ የሚገኝ የአምስተኛ ክፍል ተማሪ ወደ መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት "የሚሸጋገር" ተማሪ ተደርጎ ይቆጠራል፣ ወይም ትምህርቱን ከ6-8ኛ ክፍል ትምህርት ቤት ውስጥ እየተከታተለ የሚገኝ የስምንተኛ ክፍል ተማሪ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት "የሚሸጋገር" ተማሪ ተደርጎ ይቆጠራል። ሆኖም በአንዳንድ ሁኔታዎች ትምህርታቸውን በECE-8 ትምህርት ቤቶች እየተከታተሉ የሚገኙ የአምስተኛ ክፍል ተማሪዎች እና ትምህርታቸውን በ6-12ኛ ክፍል ትምህርት ቤቶች እየተከታተሉ የሚገኙ የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች ከፍተኛው የክፍል ደረጃ ላይ ባይደርሱም "የሚሸጋገሩ" ተማሪዎች ተደርገው ይቆጠራሉ። የሚሸጋገሩ ተማሪዎች ወላጆች/አሳዳጊዎች ከዙር 1 ቀደም ብሎ ለቀጣዩ የትምህርት ዓመት ትምህርት ቤት ለመምረጥ ምን እርምጃዎችን መከተል እንዳለባቸው (ካሉ) በDPS ይገለጽላቸዋል።

## የሚሸጋገር ልጄ SchoolChoice ማመልከቻ ባያስገባ ምን ይሆናል?

በወሰን ትምህርት ቤት ውስጥ የሚኖሩ SchoolChoice ማመልከቻ የማያስገቡ የሚሸጋገሩ ተማሪዎች በወሰን ትምህርት ቤታቸው ውስጥ ይመዘገባሉ። በምዝገባ ዞን ውስጥ የሚኖሩ SchoolChoice ማመልከቻ የማያስገቡ የሚሸጋገሩ ተማሪዎች ለዙር 2 የኦንላይን የምርጫ ማመልከቻ መሙላት ይኖርባቸዋል። የ"መረጡት" ትምህርት ቤት ከወሰን ትምህርት ቤትዎ ወይም የምዝገባ ዞንዎ ውጭ የሆነ ሌላ ትምህርት ቤት ከሆነ የአሁኑ የምዝገባ ትምህርት ቤትዎ አዲሱ ትምህርትዎን የሚከታተሉበት ትምህርት ቤት ነው። ልጅዎ በትምህርት ቤቱ ወይም ፕሮግራሙ የሚገኘውን ከፍተኛ የክፍል ደረጃ ካጠናቀቀ ወይም ልጅዎ በቀጣዩ ዓመት ትምህርቱን በሌላ ትምህርት ቤት ለመከታተል ከፈለገ ተማሪው SchoolChoice መልከቻ ማስገባት አለበት። ተማሪዎች ባለው ቦታ ላይ ተመስርቶ ትምህርት ቤት ይመደብላቸዋል።

## የ"መሸጋገሪያ የክፍል ደረጃ ላይ ያልሆኑ" ተማሪዎች፣ ለምሳሌ የሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች በSchoolChoice አሰራር ላይ መሳተፍ ይችላሉ?

አዎ። በአሁኑ ወቅት ከተመዘገቡበት ትምህርት ቤት ውጭ ሌላ ትምህርት ቤት ለመምረጥ የሚፈልጉ ተማሪዎች የ SchoolChoice ማመልከቻ ማስገባት አለባቸው።

## ማስታወስ የሚኖሩብኝ አስፈላጊ ቀናት የትኞቹ ናቸው?

- ጃንዋሪ 13፣ 2023፥ የዙር 1 SchoolChoice 10 a.m ሰዓት ላይ ይከፈታል
- ፌብሩዋሪ 14፣ 2023፥ SchoolChoice ይዘጋል። ሁሉም ማመልከቻዎች እስከ 4 p.m. ሰዓት ይዘጋሉ።
- ማርች 2023 መጨረሻ ላይ፥ ለቤተሰቦች የትምህርት ቤት ምደባዎች ይገለጹላቸዋል
- ኤፕሪል 2023 መጀመሪያ ላይ፥ የዙር 2 SchoolChoice ይከፈታል

## የ SchoolChoice ማመልከቻ የሚቀርበው መቼ ነው?

የ SchoolChoice ማመልከቻ ከጃኑዋሪ 13, 2023 ላይ በ 10 a.m. ሰዓት ጀምሮ በኦንላይን ይቀርባል። እንዴት እንደሚያመለክቱ ጨምሮ ስለ SchoolChoice የተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ሂደቱ እየተቃረበ በሚሄድበት ወቅት በ schoolchoice.dpsk12.org ላይ ይቀርባል።

## የ SchoolChoice ማመልከቻ የማስገባው የት ነው?

አሁን የDPS ኦንላይን፣ ለሞባይል ተስማሚ የ SchoolChoice ማመልከቻ አምስት አመት ሞልቶታል። ማመልከቻውን እዚህ ላይ ያገኛሉ። የምርጫ ሂደቱ ሲከፈት ቤተሰቦች የወላጅ ፖርታል አካውንታቸውን ዝርዝሮች በመጠቀም ወይም አዲስ አካውንት በመፍጠር መመዝገብ፣ ማመልከቻውን መሙላት እና በምርጫ ጊዜው ውስጥ በየትኛውም ጊዜ ማስገባት ይችላሉ።

## በ SchoolChoice ምዝገባ አሰራር ውስጥ የሚካተቱት የትኞቹ ትምህርት ቤቶች ናቸው?

የአካባቢ ትምህርት ቤቶችን፣ ልዩ ፕሮግራሞች ያሏቸው ትምህርት ቤቶችን፣ የፈጠራ ትምህርት ቤቶችን እና የቻርተር ትምህርት ቤቶችን ጨምሮ ሁሉም ማለት በሚቻል ደረጃ የዲስትሪክት ትምህርት ቤቶች በ SchoolChoice አሰራር ውስጥ ይሳተፋሉ። የመስመር ትምህርት ቤቶች በዋናነት አይሳተፉም። እባክዎ የምዝገባ መረጃ ለማግኘት በቀጥታ እነዚህን ትምህርት ቤቶች ያናግሩ።

## የምዝገባ ዞን ምንድን ነው?

በDPS ውስጥ የምዝገባ ዞን በዞኑ ውስጥ ነዋሪ ለሆኑ ተማሪዎች በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ ብቻ ሳይሆን ካሉት የተለያዩ ትምህርት ቤቶች መካከል በአንዱ ውስጥ ወንበር ማግኘታቸው የሚረጋገጥበት ጂኦግራፊያዊ ቦታ ነው። በጋራ ተደራሽ ዞን ውስጥ የሚከተሉትን ጨምሮ የተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች አሉ፥ ከፍተኛ አፈጻጸም ላላቸው ትምህርት ቤቶች ተደራሽ መሆንን፣ የትራንስፖርት አማራጮችን የማግኘት ከፍተኛ እድልን፣ የቦታው ነዋሪ ካልሆኑ ተማሪዎች ይልቅ ቅድሚያ ማግኘትን እና ለተለያዩ የትምህርት ቤት ፕሮግራሞች ተደራሽ መሆንን። ስለምዝገባ ዞኖች የተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ይመልከቱ።

## የተወሰኑ ትምህርት ቤቶች ማንኛውም ተጨማሪ የምዝገባ ደረጃዎች አሏቸው?

ጥቂት ልዩ ፕሮግራሞች ያሏቸው ትምህርት ቤቶች የ SchoolChoice ቅጽን ከመሙላት ባሻገር ተጨማሪ የብቁነት የምዝገባ ደረጃዎች አሏቸው። ለምሳሌ፣ Denver School of the Arts (ዴንቨር የስነ ጥበባት ት/ቤት) እንደ ተማሪ ማመልከቻ አንድ ክፍል የድምጽ ሙከራ ይጠይቃል። እነዚህ ትምህርት ቤቶች በ [የተመራጭ ትምህርት ቤቶች የምዝገባ መመሪያዎች] እና በ SchoolChoice ማመልከቻ ላይ ተለይተው ይገለጻሉ።

## የሁሉም ትምህርት ቤቶች የጊዜ ሰሌዳ ተመሳሳይ ነው?

አዎ። የሁሉም ትምህርት ቤቶች የ SchoolChoice ማመልከቻዎችን ማስገቢያ ማብቂያ ቀነ ገደቡ ፌብሩዋሪ 14, 2023 በ 4 p.m. ሰዓት ነው። ለቤተሰቦች የልጆቻቸው የትምህርት ቤት ምደባ በኤፕሪል ወር መጨረሻ 2023 ይገለጽላቸዋል። እንደ የአርቶች ትኩረት፣ ባለ ሁለት ቋንቋ ወይም የባለ ከፍተኛ ባለተሰጥኦ እና ባለችሎታ ፕሮግራሞች የመሳሰሉ አንዳንድ ልዩ ፕሮግራሞች ተጨማሪ የምዝገባ ደረጃዎች ያሏቸው ሲሆን እነዚህን ደረጃዎች ማጠናቀቂያ የተለዩ የጊዜ ሰሌዳዎች አሏቸው። ልዩ ትምህርት ቤት ወይም ፕሮግራም የሚያስቡ ከሆነ እባክዎ ስለ ተጨማሪ የምዝገባ ደረጃዎች የተመለከቱ ዝርዝሮችን ለማግኘት ትምህርት ቤቱን ያነጋግሩ።

## የ SchoolChoice ማዛመጃ ሲስተም የሚሰራው እንዴት ነው፤ ልጄ ትምህርት ቤት የሚመዘገበው እንዴት ነው?

ተማሪዎች በ SchoolChoice ማመልከቻቸው ላይ እንደዘረዘሯቸው ምርጫዎች ላይና በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት በተቀመጡ የምዝገባ ቅደም ተከተሎች (ለምሳሌ፣ የአንድ ቤተሰብ ልጆች ወይም የDenver ነዋሪዎች) ላይ ተመስርቶ በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ለምዝገባ ከግምት ውስጥ ይገባሉ። የእያንዳንዱ ትምህርት ቤት የምዝገባ ቅደም ተከተሎች እዚህ ላይ ይገኛ። በእያንዳንዱ የቅደም ተከተል ምድብ ስር ማንኛውኝም የምድቡን "ደረጃዎች" ለመከፋፈል በጥቅሉ ቁጥር ይሰጠዋል። የ SchoolChoice ሲስተሙ ተማሪዎች የሚመዘገቡበትን ቅደም ተከተል ለመወሰን የተማሪውን ምርጫዎች፣ የትምህርት ቤቶች ቅደም ተከተሎች እና ያሉ ወንበሮችን ከግምት ውስጥ ያስገባሉ።

## በ SchoolChoice ማመልከቻችን ላይ የዘረዘርነው አንድ ብቻ ትምህርት ቤት ከሆነ ያንን ትምህርት ቤት የማግኘት ከፍተኛ ዕድል ይኖረናል?

አይ። በ SchoolChoice ቅጽ ላይ የሚዘረዘሩት ትምህርት ቤቶች ብዛት በማንኛውም የተወሰነ አንድ ትምህርት ቤት በመመደብ እድል ላይ ለውጥ አይፈጥርም። DPS እስከ 12 ትምህርት ቤቶች ድረስ እያንዳንዱን ተማሪ የመጀመሪያ ደረጃ ተመራጭ ትምህርት ቤቶቹን እንዲዘረዝር በእጅጉ ይመክራል።

## ልጇ በመጀመሪያ ምርጫ ትምህርት ቤቱ ባይመደብ ምን ይሆናል?

ልጅዎ በመጀመሪያ ምርጫ ትምህርት ቤቱ የማይመደብ ከሆነ በትምህርት ቤቱ የመጠባበቂያ ዝርዝር ላይ ይያዛል። ትምህርት ቤቱ ቦታ በሚያገኝበት ወቅት ትምህርት ቤቱ እርስዎን አነጋግሮ የመመዝገብ እድል ይሰጥዎታል። የተጠባባቂ ዝርዝርዎ የሚገኝበትን ደረጃ ለማየት ወደ [SchoolChoice አካውንትዎ] ይግቡ።

## የመጠባበቂያ ዝርዝሮች የሚሰሩት እንዴት ነው?

የተጠባባቂ ዝርዝሮች ተለዋዋጭ እንደሆኑ ማለትም በሁሉም ሌሎች የዙር 1 እና ዙር 2 አመልካቾች ድርጊቶችና ቅደም ተከተሎች ላይ ተመስርተው ወደ ላይ ከፍ ሊሉ ወይም ወደ ታች ዝቅ ሊሉ እንደሚችሉ መገንዘብ አስፈላጊ ነው። ለምሳሌ፣ ልጅዎ በአንድ ትምህርት የተያዘበት የተጠባባቂ ዝርዝር ደረጃ በዛ ትምህርት ቤት በተጠባባቂ ዝርዝር ላይ በቅድሚያ የተያዘ ተማሪ ለትምህርት ቤቱ ወንበር በማመልከቱ ምክንያት ከቁጥር ቁጥር 6 ወደ ቁጥር 7 ሊቀየር ይችላል።

ከዚህ በታች የተመለከቱት ይህ እንዴት ሊያጋጥም እንደሚችል የተመለከቱ ጥቂት ምሳሌዎች ናቸው፦

- ከትምህርት ቤት ወሰንዎ የምዝገባ ዞንዎ (የተረጋገጠ ወንበር ካገኙበት) ውጭ በሆ ትምህርት ቤት የተጠባባቂ ዝርዝር ላይ የሚያዙ ከሆነ በዛ ወሰን ወይም የምዝገባ ዞን ውስጥ ነዋሪ የሆነ አዲስ ተማሪ በተሻለ የመጀመሪያ ቅድሚያ ይሰጠዋል።
- አንድ ተማሪ ከተጠባባቂ ዝርዝር ላይ ተቀባይነት የሚያገኝ ከሆነ በተጠባባቂ ዝርዝር ላይ የተያዘ የተማሪው እህት/ወንድም በተጠባባቂ ዝርዝር ላይ ይህ አማራጭ ከሌላቸው ተማሪዎች በላይ ይያዛል።
- አንድ የትምህርት ቤት አመልካች የትምህርት ቤቱ የሙሉ ሰዓት ሰራተኛ ልጅ ከሆነ አመልካቹ በተጠባባቂ ዝርዝር ላይ ይህ አማራጭ ከሌላቸው ተማሪዎች በላይ ይያዛል።
- አንድ የትምህርት ቤት አመልካች የትምህርት ቤቱ የሙሉ ሰዓት ሰራተኛ ልጅ ከሆነ አመልካቹ በተጠባባቂ ዝርዝር ላይ ይህ አማራጭ ከሌላቸው ተማሪዎች በላይ ይያዛል።

ስለ ትምህርት ቤት ምዝገባ ቅደም ተከተሎች ተጨማሪ ይወቁ።

ከአፀደ ህጻናት እስከ 12ኛ ክፍል ያሉት የ SchoolChoice የተጠባባቂ ዝርዝሮች እስከ ሴፕቴምበር 2023 መጨረሻ ድረስ ያገለግላሉ። የECE3 እና ECE4 የተጠባባቂ ዝርዝሮች ለ 2023-24 የትምህርት አመት እስከ ኤፕሪል 2024 ያገለግላሉ።

ከተጠባባቂ ዝርዝር ላይ በከፍተኛ ደረጃ የሚመርጡት ትምህርት ቤት ወንበር የሚሰጥዎና የሚቀበሉት ከሆነ የትኛውም ከዚህ አማራጭ በታች ያሉት የትምህርት ቤት ምርጫዎች ይሰረዛሉ።

## ልጇ አሁንም በወሰናችን ትምህርት ቤት ውስጥ ቦታ ማግኘቱ ይረጋገጥለታል?

አዎ። የ SchoolChoice አሰራር በወሰን ትምህርት ቤትዎ ውስጥ ከአፀደ ህጻናት እስከ 12ኛ ክፍል ደረጃዎች የተረጋገጠ ቦታን ጨምሮ የዲስትሪክት ፖሊሲዎችን አይቀይራቸውም። ልጅዎ በምርጫ አማካኝነት ከወሰን ትምህርት ቤትዎ ውጭ በሆነ በሌላ ትምህርት ቤት ተቀባይነት የሚያገኝ ከሆነ ትምህርት ቤቱ የእርስዎ "ማረፊያ ትምህርት ቤት" ይሆን እና ከዚያ በኋላ በወሰን ትምህርት ቤትዎ ለነበርዎት ወንበር ዋስትና አይሰጥዎትም።

## በ SchoolChoice በኩል ከወሰን ትምህርት ቤቴ ውጭ በሌላ ትምህርት ቤት ከተመዘገብኩ በኋላ ወደ ወሰን ትምህርት ቤቴ መመለስ እችላለሁ?

ወደ ወሰን ትምህርት ቤትዎ ለመመለስ በኤፕሪል ወር መጨረሻ ላይ የዙር 1 ማሳወቂያ መስጠትን ተከትሎ የዙር 2 የ SchoolChoice ማመልከቻ ሊያስገቡ ይችላሉ። ሁሉም የዙር 2 ማመልከቻዎች በመጀመሪያ ላይ ወደተጠባባቂ ዝርዝር ይገባሉ። ተጨማሪ ወንበሮች የሚገኙ ከሆነ ትምህርት ቤቱ ወንበሮችን በተጠባባቂ ዝርዝር ላይ በተቀመጠው ቅደም ተከተል ላይ ተመስርቶ ይመድባል።

## ልጄ በተጠባባቂ ዝርዝር ላይ ተይዟል። ልጄ ቦታ ካገኘ ይህ የሚገለጽልኝ መቼ ነው?

የመጠባበቂያ ዝርዝሮች እስከ ሴፕቴምበር ወር መጨረሻ ድረስ ያገለግላሉ። ትምህርት ቤቶች መስጠት የሚችሉት ወንበር እንዳላቸው ሲያውቁ ለተማሪዎች በተጠባባቂ ዝርዝር ላይ በተቀመጡት ቅደም ተከተል መሰረት የሚሰጡ ይህም የትምህርት ዓመቱ ከተጀመረ በኋላ ሊጀምር ይችላል።

## ከልጆቼ መካከል የአንዱ 'ምርጫዎች' ከተረጋገጠልን የወሰን ትምህርት ቤት ውጭ ሌላ ትምህርት ቤት ከሆነ ሌሎቹ ልጆቼም ይህንኑ ትምህርት ቤት 'ሊመርጡ' ይችላሉ?

በዙር 1 ሂደት ወቅት ለአሁን እና ተመላሽ የአንድ ቤተሰብ ልጆች ከፍተኛ ቅድሚያ የሚሰጥ ሲሆን አብዛኞቹ የአንድ ቤተሰብ ልጆች ተመሳሳይ የትምህርት ቤት ምርጫ ይፈቀድላቸዋል። ሆኖም ለአንድ ቤተሰብ ልጆች በምርጫ ትምህርት ቤታቸው መመዝገብ በቦታ ውሱንነቶች የተነሳ ሁልጊዜም ማረጋገጫ ሊሰጥ አይችልም።

## ከተለያዩ ትምህርት ቤቶች ግብዣዎች መካከል መምረጥ ያለብኝ መቼ ነው?

አንዴ የዙር 1 የ SchoolChoice ማመልከቻ ከገባ በኋላ ለሚቀጥለው የትምህርት ዓመት አዲስ ትምህርት ቤት ጠይቀዋል ማለት ነው። የ SchoolChoice ማመልከቻዎን ከማስገባትዎ በፊት የትምህርት ቤት ምርጫዎችዎን በትክክለኛው ቅደም ተከተልዎን ማስቀመጥዎን ያረጋግጡ። በማርች ወር ለልጅዎ በ“በጣም ተስማሚ” የDPS ትምህርት ቤት አንድ የትምህርት ቤት ምደባ ይሰጠዋል።

## በልጄ ትምህርት ቤት ምደባ ደስተኛ ባልሆን ወይም ሀሳቤን ብቀይር ምን ይሆናል?

የዙር 2 የ SchoolChoice የዙር 1 ማሳወቂያዎች መስጠትን ተከትሎ በኤፕሪል 2023 መጀመሪያ ላይ የሚጀምር ሲሆን እስከ ኦገስት 31, 2023 ድረስ ይቀጥላል። የዙር 2 የ SchoolChoice ማመልከቻን ለሚጠይቁት ትምህርት ቤት ማስገባት አለብዎ። ተማሪዎች የወንበር መኖር እንዳለ ሆኖ በሚፈልጉት ትምህርት ቤት ቀድሞ የመጣ ቀድሞ ይስተናገዳል በሚለው መነሻነት ይመደባሉ። የዙር 2 የትምህርት ቤት ምደባ የዙር 1 ምደባን ይተካል። ቤተሰቦች በዙር 1 እና ዙር 2 ወቅት ልጃቸው የሚያመለክትባቸውን ሁሉንም ትምህርት ቤቶች በደረጃ ቅደም ተከተል እንዲያስቀምጡ የሚጠየቁ ሲሆን የትኛውም ተማሪውን ከተቀበለው ትምህርት ቤት ያነሰ ደረጃ የሚሰጠው ትምህርት ቤት ይሰረዛል።

## ልጄ ወደሚመደብበት ትምህርት ቤት የሚያመላልሰው ትራንስፖርት ያገኛል?

የመጓጓዣ አገልግሎት የማግኘት እድል የተረጋገጠ አይደለም። ተጨማሪ ዝርዝሮች ለማግኘት እባክዎ [የትራንስፖርት ድረገጹን] ይጎብኙ።

## ለትምህርት ቤት ለማመልከት ምን አይነት ሰነዶች ያስፈልጉኛል?

ቤተሰቦች የሚከተሉትን ሰነዶች ማስገባት ይኖርባቸዋል፥

- የልጅዎ እድሜ ማረጋገጫ። ተቀባይነት ያላቸው ሰነድች የልደት ማስረጃ፣ የጥምቀት ማስረጃ ወይም የሆስፒታል መዝገብ ኮፒን/ቅጂ ያጠቃልላል።
- የወቅታዊ የአድራሻ ማረጋገጫ። ተቀባይነት ያላቸው ሰነዶች ወቅታዊ የኪራይ፣ የቤት ባለቤትነት ማስረጃ ወይም እንደ ጋዝ፣ ኤሌክትሪክ፣ ውሀ ወይም ስልክ የመሳሰሉ የአገልግሎት ክፍያዎች ኮፒን/ቅጂ ያጠቃልላል።
- የአንድ ወር ገቢ ማረጋገጫ (ለ**ECE-4** ብቻ ያስፈልጋል)። ተቀባይነት ያላቸው ሰነዶች በጣም የቅርብ ክፍያ ፔይ ስተብ (በወር ከአንድ ጊዜ በላይ የሚከፈል ከሆነ ሁሉንም የወሩን የክፍያ ጉራጆች ያካቱ)፣ የላብ ዋጋ ክፍያ መግለጫ ወይም የግብር ተመላሽ ኮፒን/ቅጂ ያጠቃልላል።
- ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎችም ከቀድሞ ትምህርት ቤታቸው ከ9-12ኛ ክፍል የትምህርት ማስረጃቸውን ማቅረብ አለባቸው።

## ተጨማሪ ጥያቄዎች ቢኖሩኝ ማንን ማነጋገር ይኖርብኛል?

የምዝገባ አገልግሎቶችን በስልክ ቁጥር 720-423-3493 ወይም በschoolchoice@dpsk12.org ማግኘት ይቻላል።